## በቶኪዮ ኢፌዲሪ ኤምባሲ የሚሰጡ የቆንስላ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች

### አዲስ ፓስፖርት ለማግኘት

- የሌላ አገር ዜግነት አለማግኘታቸውን የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ፣
- ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ፣( የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ፣ ከወረዳ የተሰጠ የነዋርነት ማስረጃ ወዘተ)
- የተሞላ የፓስፖርት መጠየቂያ ፎርም ፣
- የጣት አሻራ መስጠት፣ በኤምባሲው ቀርበው ወይንም በአከባቢው ፖሊስ የተዘጋጀ (ቀደም ሲል ፓስፖርት ሲያወጡ የጣት አሻራ ከሰጡ በድጋሚ መስጠት አያስፈልግም) ከ14 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት የጣት አሻራ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡
- አራት መጠኑ 3X4cm የሆነ ፎቶግራፍ፣
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

### በጠፋ ወይም በተበላሸ ፓስፖርት ምትክ ለማግኘት

- ፓስፖርቱ መጥፋቱን የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ፣
- የተሞላ የፓስፖርት መጠየቂያ ፎርም 2 ኮፒ፣
- የጠፋ ፓስፖርት ኮፒ ቢያቀርቡ የተሻለ ሲሆን ይህ ካልሆነ ሌላ ተጨማሪ መረጃ መረጃ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡
- የጣት አሻራ መስጠት፣ በኤምባሲው ቀርበው ወይንም በአከባቢው ፖሊስ የተዘጋጀ (ቀደም ሲል ፓስፖርት ሲያወጡ የጣት አሻራ ከሰጡ በድጋሚ መስጠት አያስፈልግም) ከ14 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት የጣት አሻራ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡
- ፓስፖርቱ የጠፋ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ፣
- አራት መጠኑ 3x4cm የሆነ ፎቶግራፍ፣
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

### የቀድሞ ፓስፖርት ለማደስ

- የሌላ አገር ዜግነት አለማግኘታቸውን የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ፣
- የተሞላ የፓስፖርት ዕድሳት መጠየቂያ ፎርም 2 ኮፒ፣
- የሚታደሰው ፓስፖርት ዋናውና 2 ኮፒ፣
- አራት መጠኑ 3x4cm የሆነ ፎቶግራፍ ማቅረብ፣
- የጣት አሻራ፣በኤምባሲው ቀርበው ወይንም በአከባቢው ፖሊስ የተዘጋጀ (ቀደም ሲል ፓስፖርት ሲያወጡ የጣት አሻራ ከሰጡ በድጋሚ መስጠት አያስፈልግም) ከ14 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት የጣት አሻራ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

### ሊሴ ፓሴ ለማግኘት

- ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃና የጽሁፍ ማመልከቻ፣
- የተሞላ የሊሴ ፓሴ መጠየቂያ ፎርም፣
- አራት መጠኑ 3x4cm የሆነ ፎቶግራፍ ማቅረብ፣
- የጣት አሻራ፣
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

### ሰነድ ማረጋገጥ

- የፓስፖርት ፎቶኮፒ፣
- የተሞላ የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም፣
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

ማሳሰቢያ 1:- የሰነድ መረጋገጫ አገልግሎት ለማግኘት በቅድሚያ የሰነዱ ምንጭ ከኢትዮጵያ ከሆነ ለኤምባሲው ከመቅረቡ በፊት በኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤እና ምንጩ ከጃፓን አገር ከሆነ በአገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፡፡

## የውክልና አገልግሎት

- የፓስፖርት ፎቶኮፒ፣
- የተሞላ የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም፣
- የተዘጋጀ የውክልና ሰነድ፣ (ናሙናውን ለማግኘት ከላይ በPDF የተጫነውን ያውርዱ)
- የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣

ማሳሰቢያ2፡-

1. የፓስፖርት ማመልከቻ ወደ ኢሚግሬሽን ዋና መምሪያ ተልኮ ተሠርቶ እስከሚመለስ ድረስ እስከ አንድ ወር ከሁለት ሳምንት ድረስ ልቆይ ይችላል፡፡
2. የሰነድ ማረጋገጥ እና የውክልና አገልግሎቶችን አስፈላጊውን ሰነድ አሟልቶ ካቀረቡ ከ20 ደቂቃ እስከ 30 ደቂቃ መካከል አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የአገልግሎት ክፊያዎቹን በተመለከተ ድረ-ገጹን ይጎብኙ!!**